**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት**
**The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order**
www.ethiopianorthodox.org

## የእመቤታችን ስደት

የሰብአ ሰገልን ገጸ በረከት
የእረኞቹን የዝማሬ አንደበት
የከብቶቹን ሙቀት መስጠት

የመላእክቱን ምስጋና
የካህናቱ ጣዕመ ዜማ
የምስራቅ ኮከብን ግርማ
የዓለም ንጉሥ ክርስቶስን መወለድ ሲሰማ፤

ሄሮድስ በምቀኝነት ተነስቶ
ልጅሽን ሊገድለው ከአንቺ ለይቶ
እልፍ አእላፋት ሕጻናትን አስፈጅቶ፤

ቢያስብም አልቀናው ይህ ዕቡይ ንጉሥ
መልአኩ ፈጥኖ ዮሴፍ ዘንድ ሲደርስ
ሕልሙን ፈቶለት ሄደ እንዲገሰግስ።

እመብርሃን ከሀገሯ ወጥታ
ዮሴፍና ሰሎሜን አስከትላ
ስትገባ በስደት ተርታ
እግሯን ሲወጋት እሾህ አሜከላ

አቤት ድንግል ጸንታ መታገሷ
መከራውን ሁሉ ችላ ማለፏ

ውኃ ቢጠማት አፏ ደርቆ
ረሃብ ጸንቶባት ሰውነቱ ደቆ፤

ጉራ ብትል እመንደሩ
ለመላቀቅ ከችግሩ፤

ማን ሰምቷት ማንስ አዝኖላት
እህል ውኃ የሚሰጣት
ከድካሟ የሚያሳርፋት

ትእማንና ኮቲባን ብትጠይቃቸው
ደጃቸው ቆማ ብትለምናቸው
ተዘከሩኝ ብትላቸው
ጥፊና ስድብ ሆነ መልሳቸው።

ፀሐይ ሐሩሩን ችላ
ድምፀ አራዊትን ታግሣ

ዝናብና ዶፍ ሲወርድባት
ብርድና ውርጭ ሲገርፋት

ስትወድቅ ስትነሳ
ግርማ ሌሊቱን አልፋ

እግሯ ሲቃጠል በበረሃው አሸዋ
አቤት ድንቅ ነው የድንግል አደራዋ
ለኛ ያደረገችው ውለታዋ
ሄሮድስ እንዳይገድለው ጥበቃዋ።
መድኅኑን በበረሃ መሸሸጓ።

ኃይለ መስቀል ተስፋዬ
ለንደን
ጥቅምት 14 ቀን 1996